በህይወታችን ውስጥ ልናውቀው የሚገባ አስፈላጊ ትምህርት ቢኖር ህይወታችን ሲያበቃ ምን ይፈጠራል የሚል ነው። ነገር ግን በቤተክርስቲያን ውስጥና ከቤተክርስቲያን ውጪ ያሉት ሰዎች ሞትን በተመለከተ ብዙ ውዥንብሮች ይነሳሉ። ሰዎች ይህንን አስፈላጊ የሆነውን ትምህርት ለመረዳት ይቸገራሉ። ምናልባትም ላለመረዳታቸው ትልቁና ዋንኛው ምክንያት ሞትን ስናስብ ደስ የማይሉ ነገሮችን አብረን ስለምናስብ ሊሆን ይችላል። በእኛ ባህል ሰው ሲሞት ቶሎ ይገነዝና ቀበራል። ምክንያቱም ስለምንወዳቸውና ስለሚወዱን ሰዎች ማሰብ አንፈልግም። ነገር ግን ይህንን ርዕስ በደንብ ልናተኩርበትና ልናጠና ያስፈልጋል ምክንያቱም ዘላለማዊ ህይወት ካለን ሞት የሚባለው ነገር መልካም ዜና ይዞልን ይመጣል።

ሰዎች ከሞት በኋላ ምን ይፈጠራል ብለው ውዥንብር ውስጥ ሲገቡ ማየት ብዙም አዳጋች አይሆንም። በመቃብር ላይ የሚፃፉ ጽሑፎችን ስንመለከት ለዚህ ውዥንብር መባባስ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ለምሳሌ አንዱ መቃብር ላይ "አባቴ በክርስቶስ እጅ አርፎ የትንሳኤ መለከት ለመስማት እየተጠባበቀ ይገኛል።" የሚሉና ሌሎች ላይ ደግሞ "እናቴ በሰማይ በወርቁ ጐዳና ላይ ከመላዕክቶች ጋር እየዘመረች ነው።" ብለው ይጽፋሉ። ስለዚህ የቱ ነው? የሞቱ ሰዎች ትንሳኤን እየተጠባበቁ ናቸው ወይስ ሌላ ቦታ በህይወት አሉ? ሌላ ቦታ ከሆኑ ምን እየሰሩ ነው? ጥሩ እና ታማኝ በሆኑት ክርስቲያኖች እንኳን ሳይቀር ይህ ክርክር አለ። ይህ ሰለ ሞት የምናጠናው ጥናት በሰው ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆነ ማስረጃ ከሚሰጠን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናጠናለን።

## ህይወትና የሰው ነፍስ

ከሞት በኋላ ምን እንደሚከሰት ከማጥናታችን በፊት ህይወት የሚባለው ነገር እንዴት መጣ የሚለውን ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል። በኤዴን ገነት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሲፈጥር ሰው ህያው ነፍስ ሆነ። "እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው በአፍንጫውም የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ህያው ነፍስ ሆነ።" ዘፍ 2፡7 አስተውሉ እግዚአብሔር "ለሰው ነፍስ ሰጠ" አይልም ነገር ግን "ሰውም ህያው ነፍስ ሆነ" ነው የሚለው። ከመሬት አፈር ወስዶ (ሰውነታችን) አስፈላጊ የሆነውን ከእግዚአብሔር የህይወት እስትንፋስ ጋር በማገናኘት ነፍስን ፈጠረ። እንግዲህ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ድርጊቱ የተገላቢጦሽ ይሆናል ማለት ነው። "አፈር ወደ መጣበት መሬት ሳይመለስ መንፈስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ።" መክብብ 12፡7 እንግዲህ ይህ ማለት በእግዚአብሔር የተሰጠች መንፈስ (ዘፍጥረት 2፡7) ወደ እግዚአብሔር ስትመለስ አንድ ሰው ሞተ እንላለን።

"በውስጤ የህይወት እስትንፋስ፣ በአፍንጫዬም ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ እስካለ ድረስ" ኢዮብ 27፡3። እዚህ ላይ እዮብ እየተናገረ ያለው "የህይወትን እስትንፋስ" በዘፍጥረት 2፡7 ላይ ያለውን ነው። በእብራይስጠኛም ተመሳሳይ ቃል ነው የሚጠቀመው። ስለዚህ ሰው ሲሞት ሰውነታችን ወደ አፈር ይመለሳል የህይወት እስትንፋስ ደግሞ ወደ ሰጪው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል ማለት ነው። የዛኔ ህይወት የሚባል ነገር ያቆማል።

## ከህይወት በኋላ ዘላለማዊ ስጦታ

ዛሬ ማንም ሰው በሲኦል እየተሰቃየ ሌላው በሰማይ እየተደሰተ ያለ ሰው የለም። ምናልባት ይህ አስደንጋጭ ሊሆን ይችላል ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የምያስተምረው ይህንን ነው።

"እነሆ ቶሎ እመጣለው ዋጋዬ በእኔ ዘንድ አለ ለእያንዳንዱም እንደ ስራው መጠን እከፍለዋለው" ራዕ 22፡12። ሁሉም ሰው ዋጋውን የሚያገኘው ክርስቶስ ሲመለስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ እስካሁን አልተመለሰም። ተመልሷል? ይህንን መገንዘባችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው የፍርዱ ሰዓት ደርሷልና።

"እንደዚሁም ሰው ይተኛል ቀናም አይልም ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ አይነቃም ከእንቅልፉም አይነሳም" ኢዮብ 14፡12። ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ ሙታን በመቃብራቸው አይነሱም። ሰማይ የሚያልፈው መቼ ነው?

"ጌታ ቀን እንደ ሌባ ይመጣል በዚያች ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ የሰማይ ፍጥረት በእሳት ይጠፋል ምድርና በእርሷ ያለ ነገር ሁሉ ይቃጠላል" 2ጴጥ 3፡10። ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ በዚያ ቀን ሰማያት ያልፋሉ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን ሙታን ከመቃብራቸው አይነሱም።

## ግን አሁን ሰዎች በሰማይ የሉም?

አዎ ጥቂቶች አሉ። ግን የተወሰኑት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የመለወጥን ታሪክ ይነግረናል። ክርስቶስ በተራራ ጫፍ ላይ ሙሴና ኤልያስ ተገልጦለት ነበሩ። በእውነተኛ ስጋቸው ተገልጠው ነበረ። ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ ደቀ መዛሙርቱም አይቷቸው ነበሩ። እየሱስን ልያደፋፍሩት ከሰማይ መጡ። ነገር ግን እንዴት ወደ ሰማይ ወጡ?

በ2ነገ 2፡11 ላይ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ እንደተወሰደ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ኤልያስ ወደ ሰማይ ሲሄድ ሞትን አልቀመሰም ነበረ። ሙሴም መጀመሪያ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር አስነሳውና ወደ ሰማይ ወሰደው (ይሁዳ 9)

በማቴዎስ 27 ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ሳለ ታላቅ የመሬት መናወጥ ሆነ። መቃብሮችም ተከፈተው ነበረ። ከክርስቶስ በፊት የነበሩ ብዙ አበውና ነቢያት በተለየ ትንሳኤ ተነስተው ነበረ። እዚያ ቦታ ላይ ስማቸውም አይዘረዝም ስለዚህ እነማን እንደሆኑ በትክክል አናውቅም። ግን በክርስቶስ ትንሳኤ ከመቃብር ተነስተው ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ሄዱ። አንደኛ በክርስቶስ ትንሳኤ ከእርሱ ጋር ተነስተው ነበረ። ሁለተኛ ይህ የሰዎች ትንሳኤ የክርስቶስ የተልዕኮው የመጀመሪያዎቹ ፍሬዎች ናቸው ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅስ ነው።

## ባዶ መቃብሮች

ወደ መቃብር ቦታ ስትሄዱ የፍርሃትና የድንጋጤ ስሜት አይሰማችሁም? በተለይ ፀሐይ ስትጠልቅ የተለየ መንፈስ ከመቃብር ተነስቶ የሚያንቃችሁ አይሰማችሁም? በእኛ ባህል ውስጥ እንደዚህ አይነት ድርጊቶች እንዳሉ ተምረን አድገናል እንዲሁም ሙታ እንዳልሞቱ ተነግሮናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሞቱ ሰዎች ከመቃብር እንዳልተነሱ ያስተምረናል።

ከመኝታ ቤታችሁ ነቅታችሁ ለጥቂት ጊዜ እንደተኛችሁ ይሰማችሁና ሰዓታችሁን አንስታችሁ ስትመለከቱ ብዙ ሰዓት እንደተኛችሁ ተሰምቶአችሁ አያውቅም? በእንቅልፍ ውስጥ ሆናችሁ የተኛችሁት ሰዓት አታውቁም። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ነው የሞትን መጽሐፍ ቅዱስ እንቅልፍ የሚለው። ለዳኑትና የጠፉትንም ተመሳሳይ ነው።

"እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ተመልከት ስማኝም የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ አይኖቼን አብራ"መዝ 13፡3። በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳንም ይሆን በብሉይ ኪዳን በተዳጋጋሚ ሞትን ከእንቅልፍ ጋር ያመሳስለዋል። እየሱስ ስለ አልዓዛር ሲናገር ሞትን ከእንቅልፍ ጋር ያመሳስለዋል። "ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአልና እኔም ከእንቅልፉ ላስነሳው እሄዳለው አላቸው" ዮሐ 11፡11። ደቀ መዛሙርት ግን ያስተዋሉት በጥሬ ቃሉ ነበረ ነገር ግን ክርስቶስ ሰለ አልዓዛር ሞት እንደሚናገር ገለጸላቸው።

እየሱስ ወደ አልዓዛር መቃብር ሲሄድ አራት ቀን አልፎት ነበረ። የአልዓዛር አስከሬን መበስበስ ጀምሯል ወደ አፈርነት እየተለወጠ። መቃብሩ እራሱ እንዳይከፍት ማርታ ፈልጋ ነበረ። ከዚያ እየፈሩ ድንጋዩን አንከባለሉት እየሱስም በታላቅ ድምጽ ጮኸ እንዲህ ሲል "አልዓዛር ውጣ" አልዓዛርም ወጣ። ምናልባት ይህ ክስተት አሁን ተከስቶ ቢሆን የተለያዩ አለም አቀፍ የዜና አውታሮች አልዓዛርን ጠርተው ቢያነጋግሩት ምን አይነት ጥያቄ ይጠይቁት ነበረ?

አንዳንዶች ሰውነታችን ሲጠፉ ነፍሳችን እንደማትጠፋ አድርገው ያስባሉ። ግን መጽሐፍ ቅዱስ በመክብብ 9፡5-6 "ህያዋን እንደ ሚሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን ምንም አያውቁምና መታሰቢያቸው ይረሳል ምንም ዋጋ የላቸውም። ፍቅራቸው፣ ጥላቻቸው፣ ቅናታቸው፣ ከጠፉ ቆይቶአል ከፀሐይ በታች በሚሆነው ነገር ሁሉ ፈፅሞ ዕጣ ፋንታ አይኖራቸውም።"

## ሙታንን ማናገር

ጳውሎስ ሞትን በተመለከተ ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል "ወንድሞች ሆይ አንቀላፍተው ስላሉ ሰዎች ሳታውቁ እንዳትቀሩ አንፈልግም... " 1ተሰ 4፡13። ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች ስለ ሙታን ሁኔታ እንዲያውቁና እንዲረዱ ፈልጐ ነበረ ምክንያቱም ይህንን አለማወቅ በመጨረሻ ዘመን ወደ ስህተት እንደሚመራ ያውቅ ነበረ። ስለሙታን ሁኔታ የሚናገሩ ከ100 በላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ ነገር ግን ምን ያህል ነው ሰዎች በዚህ ርዕስ ላይ የሚሳሳቱት "በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች እምነትን ከደው አታላይ መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት እንደሚከተሉ መንፈስ በግልጥ ይናገራል።" 1ጢሞ 4፡1

## ስለሙታን ሁኔታ ማወቁ ለምን አስፈለገ?

“እግዚአብሔር ‘እንዴት አድርገህ?’ ሲል ጠየቀው። እርሱም ‘እኔ እወጣለሁ በገዛ ነቢያቱም አፍ ሁሉ የሐሰት መንፈስ እሆናለው’ አለ” 1ነገ 22፡22። በመጨረሻ ዘመን የሐሰት መንፈስና ሐሰተኛ ነቢያቶች ተነስቶአል። ራዕይ 16 ላይ እነዚህ እርኩስ መናፍስት ወደ ታላላቅ የምድር ነገስታት ይወጣሉ ድንቅና ታምራትን ይሰራሉ ብዙዎችንም ያስታሉ። ይህ የሐሰት ትምህርት ብዚዎች በአጋንንት ትምህርት እንዲያምኑ ያደርጋሉ ይህም የሙታንን መንፈስ ብዙዎችን በማሳት ከክርስቶስ መንገድ ይለያቸዋል።

“ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነብያት ይነሳሉና ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምልክቶችንንና ታምራትን ያደርጋሉ።” ማቴ 24፡24

ይህንን በመጨረሻ ዘመን ላይ የሚመጣው የሐሰት ትምህርት እንዴት ማምለጥ እንችላለን? “የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክንያቱም ነገሩ እንዲህ ይሆንን እያሉ ቃሉን በታላቅ ጉጉት ተቀብለዋል” የሐዋ 17፡11። የእግዚአብሔር ቃል የማንነታችን መሰረት ሊሆን ይገባል። “... እነርሱም እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ የንጋት ብርሃን የላቸውም።” ኢሳ 8፡20

ማንም የሞተ ሰው ለእናንተ ከተገለጠ (ከታየ) ከሰይጣን ወይም ከአይምሮአችሁ በትክክል በለማይሰራ መሆን አለበት።

የፃድቃን ጥሪ

“ጌታ እራሱ በታላቅ ትዕዛዝ በመላዕክት አለቃ ድምጽና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳልና። በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድሞ ይነሳሉ”። 1ተሰ 4፡16 እየሱስ በግልጽ እንዳስቀመጠው ይህ ትንሳኤ በመጨረሻ ጊዜ የሚሆን ትንሳኤ ነው።

“በዚህ አትደነቁ መቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል መልካም የሰሩ ለህይወት ትንሳኤ ክፉ የሰሩ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉ” ዮሐ 5፡28-29።

“... በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም እንዲኖረው ነው እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሰዋለው” ዮሐ 6፡40። እዚህ ላይ ከሞቱት ሰዎች ውስጥ ስንቱ ተነሱ? ማንም አልተነሳም። የዳኑት ሰዎች በመጨረሻ ቀን ላይ ይነሳሉ።

በተጨማሪም “ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ህያዋን ይሆናሉ። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኩራት የሆነው ክርስቶስ፣ ከዚያም በኋላ እርሱ እስኪመጣ የክርስቶስ የሆኑት” 1ቆሮ15፡22-23። ክርስቶስ ሲመጣ እርሱን ያመኑት ሰዎች ይነሳሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይገባልናል አንድ ቀን “እንባን ሁሉ ከአይናቸው ያብሳል ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ለቅሶ ወይም ስቃይ አይኖርም የቀድሞ ስርአት አልፎአልና” ራዕ 21፡4

በሚያሳዝን ሁኔታ ሞት አሁን በአለማችን ያለ እውነታ ነው። ይህ ደግሞ ስለ ሞት እንድንጨነቅ እና ሞትን እንድንፈራ ያደርገናል። ነገር ግን ስለሞት አለመጨነቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። ክርስቶስ ቃል ገብቶልናል “ልጁ ያለው ህይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም” 1ዮሐ 5፡12

ክርስቲያኖች ለዘላለም ስላልሞቱ እንዲህ ያለ ህይወት አሁን ይጀምራል። ምናልባት ለትንሽ ጊዜ ህልም አልባ እንቅልፍ ትተኙ ይሆናል ግን በዛ በታላቁ ቀን ክርስቶስ መጥቶ ይቀሰቅሳችሁዋል። ክርስቶስ ካለዎት ስለ ሞት አይጨነቁ ስለዚህ የቃሉን ሙላትና የእርሱን ጽድቅ በህይወትዎ እንዲቀበሉ እጋብዞታለው።